# Lynnwood Link Connections
# የምዕራፍ 2 የህዝብ ተሳትፊ ማጠቃለያ

ጃንዋሪ-ማርች 2023

## የምዕራፍ 2 ተሳትፎ - የአገልግሎት ጽንሰ ሃሳቦች

*የተካሄደው ጃንዋሪ-ማርች 2023*

### ግቦች

የምዕራፍ 2 ተሳትፎ አላማ ስለ አገልግሎት ጽንሰ ሃሳብ አውታረ መረብ— በተጨናነቀ አካባቢ ያሉ ማህበረሰቦች አሽከርካሪዎችን ጨምሮ— ለጠቅላላው ህዝብ ማሳወቅ እና የመንገዶቹ ጽንሰ ሃሳብ ለቀዳሚ የእንቅስቃሴ ፍላጎቶች እንዴት መፍትሄ እንደሚሰጡ ግብረ መልስ ለመሰብሰብ ነበር። የአገልግሎት ጽንሰ ሃሳቦች የአውታረ መረብ እቅድ በፕሮጀክት አካባቢ ውስጥ የእንቅስቃሴ አማራጮችን በተሻለ ሁኔታ ለመደገፍ በ Metro የተነደፉ እና የምዕራፍ 1 ቀዳሚ የእንቅስቃሴ ፍላጎቶችን በመጠቀም የታቀዱ የአውቶቡስ መስመሮችን ይዟል። በምዕራፍ 2 የአገልግሎት ጽንሰ ሃሳቦች ላይ የተለየ አስተያየት በመቀበል፣ Metro ስለ ማህበረሰብ ፍላጎቶች እና የመጨረሻውን የአውቶቡስ መስመሮች ፕሮፖዛል ለደረጃ 3 የማህበረሰብ ተሳትፎ እንዴት ማሳወቅ እንዳለባቸው የበለጠ ማወቅ ይችላል።

የግንዛቤ፣ ተሳትፎ እና የግብረ መልስ ግምገማ የድርጅቱ የደንበኛ ቡድን ወሳኝ አካል በሆኑት በ Metro ቅድሚያ የሚሰጣቸው ህዝቦች[1] ላይ ትኩረት ማድረግን ያካትታል። የፕሮጀክት ማስረጃዎች እና 2 ዳሰሳ ጥናት በ11 ቋንቋዎች ይገኛሉ

የህዝባዊ ተሳትፎ ምዕራፍን ተከትሎ፣ የ Mobility Board (የእንቅስቃሴ ቦርድ) እና Partner Review Board (አጋር የግምገማ ቦርድ) የማህበረሰብ ግብረ መልስ የበለጠ ቅድሚያ እንዲያገኝ የረዱ ሲሆን የደረጃ 3 የአገልግሎት ፕሮፖዛልን ለማዘጋጀት ጥቅም ላይ የሚውሉ ጠቃሚ የንግድ ልውውጦችን ተወያይተዋል። Mobility Board ቦርድ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ደረጃዎች ከታች ባለው ቻርት ላይ ይታያሉ።

እንዲሁም የ Metro ሰራተኞች ከማህበረሰብ ቡድኖች፣ በአካል በመገናኘት የተሰጠ ጥራት ያለው ግብረ መልስ፣ ከዳሰሳ ጥናቱ ውጪ ለሜትሮ የቀረቡ አስተያየቶችን፣ የትኩረት ቡድኖችን እና ሌሎች ስብሰባዎችን ገምግመዋል። ይህ ግብረመልስ በሚታወቅበት ጊዜ ቅድሚያ በሚሰጠው ህዝባዊ ሁኔታ አማካኝነት ተመድቧል።

---

[1] *ቅድሚያ የሚሰጣቸው ህዝቦች $35,000 ወይም ከዚያ በታች ገቢ ለው ቤተሰብን፣ አካል ጉዳተኛ የሆኑ፣ ስደተኞች ወይም ጥገኞችን፣ በቤት ውስጥ ከእንግሊዝኛ ሌላ ቋንቋ ብቻ የሚናገሩ ወይም ሂስፓኒክ ነጭ ባልሆነ ዘር እና/ወይም ጎሳ የሚለዩ የማህበረሰብ አባላትን ሊያጠቃልል ይችላል።*

## በምዕራፍ 2 ተሳትፎ የተማርነው

በምዕራፍ 2፣ Metro 3,182 የተሟላ የዳሰሳ ጥናት ምላሾች፣ እና ተጨማሪ 2,330 ከፊል ምላሾችን ተቀብሏል። ከዳሰሳ ጥናት ግብረመልስ በተጨማሪ፣ Metro በምዕራፍ 2 የአገልግሎት ጽንሰ ሃሳቦች ላይ ጥራት ያለው ግብረ መልስ በሚከተሉት አማካኝነት ተቀብሏል፦

- ከአራት ማህበረሰብ ተኮር ድርጅት አጋሮች ስርጭት እና የተሰጠ ግብረመልስ።
- ለገቢ ብቁ የሆኑ የመኖሪያ ቤት አቅራቢዎች፣ የትምህርት ተቋማት፣ የአካባቢ ቡድኖች፣ የከተማ ምክር ቤቶች፣ የተመረጡ መሪዎች እና የመጓጓዣ አማካሪ ቡድኖችን ጨምሮ ዋና ዋና ከሆኑ ታዳሚዎች ጋር በተካሄዱ 15 ስብሰባዎች።
- በማህበረሰብ እና በመጓጓዣ ቦታዎች ከ115 ሰአታት በላይ በአካል ተገኝቶ በማሰራጨት።
- ሶስት የመስመር ላይ ምናባዊ ክፍት ቤቶች።
- በ Metro HaveASay ኢሜይል በኩል የተጻፉ አስተያየቶች።

ከዳሰሳ ጥናት ምላሽ ሰጪዎች የተመረጠ የስነ ህዝብ መረጃ የሚከተሉትን ያጠቃልላል።

- 37% ቅድሚያ የሚሰጠው ህዝብ ተለይቷል።
- 22% አካል ጉዳተኛ እንደሆኑ ተለይተዋል
- 21% ተሽከርካሪ ማግኘት እንደማይችሉ ተለይተዋል።
- ምላሽ ሰጪዎች በእድሜ፦
  - ከ 25 በታች– 10%
  - ከ 25-34 – 18%
  - ከ 35-44 – 18%
  - ከ 45-54 – 14%
  - ከ 55-64 – 12%
  - ከ 65+ – 11%
  - ባዶ – 17%
- አብዛኛዎቹ ምላሽ ሰጪዎች በሚከተሉት ከተሞች ውስጥ ይኖራሉ (አብዛኛዎቹ ምላሽ ሰጪዎች በቅደም ተከተል)
  1. Seattle
  2. Shoreline
  3. Lynnwood
  4. Bothell
  5. Lake Forest Park

ከላይ በተዘረዘረው ተሳትፎ አማካኝነት በዳሰሳ ጥናቱ የተገኘውን ግብረ መልስ እና ጥራት ያለው ግብረመልስ በመገምገም፣ Metro በጽንሰ ሃሳብ አውታረ መረቡ ውስጥ የሚሰሩ ስምንት ዋና ዋና ዘርፎችን ለይቷል። የህብረተሰቡን ግብረመልስ ለመለየት እና በተለይም ቅድሚያ በሚሰጣቸው ህዝቦች ከሚነሱ ችግሮች ጋር በተያያዘ አነስተኛ ለውጦች ሊደረጉባቸው የሚችሉ ቦታዎችም ተጠቁመዋል።

እነዚህ ስምንት ዋና ዋና ቦታዎች፣ እንዲሁም የ Mobility Board ቅድሚያ የሚሰጣቸው ደረጃዎች ከታች ባለው ቻርት ላይ ቀርበዋል።


**ቅድሚያ የሚሰጠው አጠቃላይ ማቃለል** የፕሮጀክቱን ሶስት ፍትሃዊ የውሳኔ የሚሰጥባቸው ምክንያቶችን፣ ተሳትፎን እና የመጓጓዣ አውታረ መረብ ንድፍን ያካትታል። **መፍትሄ ለመስጠት የሚያስፈልጉ የመርጃዎች ደረጃ** እያንዳንዱን ችግር ለመፍታት ከሌሎች መስመሮች ምን ያህል የመጓጓዣ አገልግሎት ሰአታት መቀየር እንዳለባቸው ይገልጻል።

## ከምዕራፍ 2 ተሳትፎ ዋና ዋና ችግር ያለባቸው አካባቢዎች

| # | ችግር ያለበት አካባቢ | ቅድሚያ የሚሰጠው አጠቃላይ ማቃለል | መፍትሄ ለመስጠት የሚያስፈልጉ መርጃዎች ደረጃ | የ Mobility Board ቅድሚያ የሚሰጥበት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | በ NE 75th እና NE 92nd መካከል የ Lake City Way አገልግሎት እንቅስቃሴ | ከፍተኛ | መካከለኛ | **ከፍተኛ** |
| 2 | በ 135th የ Linden Ave አገልግሎት እንቅስቃሴ | ከፍተኛ | መካከለኛ | **ከፍተኛ** |
| 3 | በN 130th St እና 200th St መካከል የMeridian Ave አገልግሎት እንቅስቃሴ | መካከለኛ | ከፍተኛ | **ዝቅተኛ** |
| 4 | በ Green Lake Way እና NE 45th መካከል የ Latona Ave አገልግሎት እንቅስቃሴ | ዝቅተኛ | መካከለኛ | **ዝቅተኛ** |
| 5 | በ NE 125th እና NE Northgate Way መካከል የ 5th Ave NE አገልግሎት እንቅስቃሴ | ከፍተኛ | መካከለኛ | **ከመካከለኛ-ከፍተኛ** |
| 6 | የRoute 75 ለውጥ ከNorthgate ጋር አይገናኝም | ዝቅተኛ | መካከለኛ | **ዝቅተኛ** |
| 7 | ከሰሜን ምዕራብ King County እስከ First Hill ድረስ ያሉ ቀጥተኛ ግንኙነቶች መጥፋት | መካከለኛ | ከፍተኛ | **ከዝቅተኛ-መካከለኛ** |
| 8 | በአዲሱ ከBothell እስከ UW ባለው ግንኙነት አለመርካት | መካከለኛ | ከፍተኛ | **ዝቅተኛ** |

## ከምዕራፍ 2 ተሳትፎ ዋና ዋና ችግር ያለባቸው ቦታዎች ካርታ

ከላይ ባለው ቻርት በካርታው ማጠቀሻ ቁጥሮች ላይ ያሉ ቁጥሮች



## ወደ ፊት ይመልከቱ

በምዕራፍ 3፣ የመጨረሻው ዋና የህዝብ ተሳትፎ ምዕራፍ፣ ተሳትፎ የአገልግሎት ፕሮፖዛሉ ከምዕራፍ 2 ለተቀየረባቸው የተወሰኑ አካባቢዎች እና ታዳሚዎች፣ እንዲሁም የታቀዱ ለውጦች አሁን ካሉት መስመሮች በተለዩ መንገዶች የሚያገለግሉባቸው ፍትሃዊ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ቦታዎች ላይ ታቅዷል። ማህበረሰብ ተኮር ድርጅቶች፣ የመኖሪያ ቤት አቅራቢዎች፣ የትምህርት ተቋማት እና ሌሎች የተለዩ ቀዳሚ ታዳሚዎች ያሉ፣ በምዕራፍ 2 ላይ የተሳተፉ ዋና ዋና ታዳሚዎች በክፍል 3 እንደገና የሚሳተፉ ይሆናል።

እንዲሁም አጠቃላይ የህዝብ ተሳትፎ በየቀኑ ለሚያስከረክሩ እና ለነዋሪዎች የመስመር ፕሮፖዛሎችን እንዲገመግሙ እና የመጓጓዣ አውታረ መረብ ፕሮፖዛል እንዴት እንደሚያሻሻል ወይም በሌላ መልኩ አጠቃላይ የእንቅስቃሴ አማራጮችን እንደሚለውጥ አስተያየት እንዲሰጡ እድል ይሰጣል። አብዛኛው የዚህ ተሳትፎ በመጓጓዣ ቦታዎች፣ በማህበረሰብ ማዕከላት፣ በአካባቢ ዝግጅቶች እና በተለያዩ የመገናኛ መንገዶች ላይ እንደሚሆን ይጠበቃል።

በመረጡት ቋንቋ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፣ እባክዎ የኛን የ **Lynnwood Link Connections የፕሮጀክት ገጻችንን** (Lynnwood Link Connections - King County Metro Transit) **ይጎብኙ ወይም በ haveasay@kingcounty.gov ያነጋግሩን**

**Póngase en contacto con nosotros**
Por correo electrónico (en el idioma que prefiera) a: haveasay@kingcounty.gov

### 联系我们

以电子邮件（以您的首选语言）发送至：haveasay@kingcounty.gov

### 聯絡我們

通過電子郵件（以您的首選語言）發送至：haveasay@kingcounty.gov

**እኛን ያግኙን**
በሚመርጡት ቋንቋ ይህን ኢሜል ተጠቅመው haveasay@kingcounty.gov ያግኙን

### お問い合わせ先

電子メールの宛て先（ご希望の言語で）：haveasay@kingcounty.gov

### 연락처

이메일 (귀하께서 선호하시는 언어로 보내십시오): haveasay@kingcounty.gov

**Свяжитесь с нами**
Пишите нам (на удобном вам языке) на адрес электронной почты: haveasay@kingcounty.gov

**Nalasoo Xariir**
Iimeel ahaan (luuqada aad doorbido): haveasay@kingcounty.gov

**Makipag-ugnayan sa amin**
Sa pamamagitan ng email (sa wikang gusto mo) sa: haveasay@kingcounty.gov

**Liên hệ với chúng tôi**
Qua email (bằng ngôn ngữ của quý vị) tại: haveasay@kingcounty.gov